# መጪው የኢህአዴግና የተቃዋሚዎች ተስፋና ፈተና

መለስ ዓ.

አራተኛው የኢትዮጵያ ጠቅላላ ምርጫ ተጠናቅቆ የምርጫ ቦርድ ኢህአዴግ በመላ አገሪቱ ባሉ የምርጫ ክልሎች እየመራ መሆኑን አስታውቋል:: ይህ ጽሁፍ እስከተዘጋጀበት ግንቦት 25 ቀን 2002 ዓ.ም ያለው የቦርዱ ሪፖርት እንደሚያሳየው ገዢው ፓርቲ 499 ወንበሮች አሸንፏል:: ይህም ማለት ፓርቲው በ92 በመቶ አብላጫ ውጤት አግኝቷል:: በአዲስ አበባም ቢሆን ተቃዋሚዎች አንድ ወንበር ብቻ ነው ያሸነፉት:: እንደ ፀሀፊው እምነት ገዢው ፓርቲ አዲስ አበባ ውስጥ ከ1997 በተቃራኒ ያስመዘገበው ውጤት "... ማን ነሽ ባለተራ" ያሰኝ ነው:: የርዕሰ መዲናችን ነዋሪ በ3ኛው አገራዊ ምርጫ የሰጠውን ድምጽ እና የህዝብ ይሁንታን ረግጠው ያልተቀበሉ ወገኖችን ቀይ ካርድ አሳይቷቸዋል:: ኢህአዴግም ካለፈው ምርጫ ትምህርት በመቅሰም ለፈፀመው መልካም ተግባር ተሹሟል፣ ተሸልሟል:: ኢህአዴጎች ለዲሞክራሲ ፌስታውም ዋንጫ ቢያነሱ ይገባቸዋል::

## ያልተሳካው ሟርት

ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ የተባለው ተቋም ባለፈው መጋቢት ወር 2002 ዓ.ም ሀገራችንን በተመለከተ ባወጣው መግለጫ በስኬት ያካሄድነውን አጠቃላይ ምርጫ ከሁከት እና ትርምስ የፀዳ እንደማይሆን ተንብዮ ነበር:: ከዚህም በኋላ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ነን የሚሉ ድርጅቶች፣ ቢቢሲ፣ ሲኤንኤን በቅርቡ ደግሞ ሂውማን ራይትስ ዎች የመሳሰሉ ድርጅቶች በምርጫው ገዢው ፓርቲ የማሸነፍ ዕድል እንደሚኖረው ይናገሩ እንጂ በሁሉም ዘገባዎችና ሪፖርቶቻቸው ላይ ሁለት ነገሮችን ከመጥቀስ አልቦዘኑም ነበር:: የምርጫው ሂደት ተዓማኒ እንደማይሆንና እንደ 1997 ምርጫ ደም መፋሰስ እንደሚኖር ተንብየውልን ነበር:: ከእነዚህ አካላት በተጨማሪ ከምርጫ ጋር ተያይዞ ሀገራችን በደም አበላ ትታጠባለች ብለው የገመቱ ወገኖች ወገባቸውን ሲያጠብቁ ቢከርሙም ህዝባችን ንፁህና የሰለጠነ ኢትዮጵያዊነት ባህሪውን አሳይቶ አሳፍሯቸዋል::

አዲስ አበባ ውስጥ መቀመጫቸውን አድርገው የሚንቀሳቀሱ የዓለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምርጫውን ተከትሎ አለመረጋጋት እና ደም መፋሰስ ይኖራል በሚል ለሠራተኞቻቸው የ2-3 ወራት ደሞዝ ቀድመው ከፍለው እንደነበር የምናውቅ ስንቶቻችን እንሆን? በእነዚህ ድርጅቶች የሚሠሩ የውጭ ሀገር ሰዎች ስም ዝርዝርም ከሀገር ማስወጣት እንዲቻል ተለይቶ የተያዘበት ሁኔታ እንዳለ ስንገነዘብ ምን

ተደግሶልን ነበር? ያሰኛል። በአንድ የአሜሪካ አለም አቀፍ ድርጅት የሚሠራ ወዳጄ እንደነገረኝ ድርጅቱ አንድ ክፉ ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ ከተፈጠረ የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ መሹለኪያ ስትራቴጂ /Exit Strategy/ አዘጋጅቶ ይመጣል ያሉትን ክፉ ጊዜ ሲጠብቅ እንደነበር አጫውቶኛል። ከዚህ በባሰ ሁኔታ የአንድ አገር በቀል ከፍተኛ ኩባንያ አማካሪዎች ጨርቄን ማቄን ሳይሉ ከሀገር ወጥተው ሄደዋል። ይህ ግምት በምርጫው ቀን እንደጉም በኗል። ከዚህ ውል አልባ ግምት እና ፖለቲካዊ ሟርት በተቃራኒ የኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ስር እየያዘ መሆኑን በሚያሳይ ሁኔታ ምርጫው ሠላማዊ፣ ዲሞክራሲያዊ እና ፍትሀዊ በሆነ መልኩ ተጠናቋል። የኢትዮጰያ ህዝብም ለዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ያለውን ዝግጁነት ምርጫው እንዲካሄድ በማድረግ አሳይቷል። የአውሮፓ ህብረት ታዛቢ ቡድን የመጀመሪያ ጊዜያዊ ሪፖርት ላይ በይፋ እንደተገለፀው ሀገራችን ሠላማዊ እና ሰነስርዓቱን የጠበቀ ምርጫ በሠለጠነ መልኩ አካሂዳለች።

እዚህ ላይ መዳሰስ ያለበት ምርጫው ለምን በሰከነ መንፈስ ተደረገ? የሚለው ነው። እንደ እኔ እምነት ዋናው ምክንያት መራጩ ህዝብ ከ1997 ምርጫ ሂደት አያሌ ትምህርቶችን በመውሰድ እና የቂም በቀል እና የጥላቻ ፖለቲካ ለሀገራችን አይበጅም በማለት ስለተጠየፈ ተቃዋሚዎችን ቀጥቷል። ህብረተሰቡ አብዛኞቹ ተቃዋሚዎች ከተራ ስንክሳር የማውጣት አካሄድ ውጭ ይህ ነው የሚባል ለኢትዮጵያ ውስብስብ ችግሮቹ አማራጭ መፍትሄ የሚሆን ፖሊሲና ስትራቴጂ አልቀረፁም፤ በዚህ ሁኔታዎች ደግሞ ኢትዮጵያን የምታህል ታላቅ ሀገርም የመምራት ብቃት አይኖራቸውም የሚል መደምደሚያ ላይ መድረሱንም በዚህ ምርጫ አረጋግጧል። ጉልህ የሆነ የሠላምና መረጋጋት ዕጥረት በሚታየው የአፍሪካ ቀንድ ተቃዋሚዎች እንዴት ብለው ኢትዮጵያን መምራት ይችላሉ የሚለው ጥያቄ የስንቶቻችን እንደሆነ ባላውቅም ለእኔ ነገ አሳሳቢ ጉዳይ ነው። በተጨማሪም በሀገራችን ያሉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ተዋሃዱ ሲባሉ በማግሥቱ የሚፈርሱ፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት የሌላቸው መሆናቸውም ለሽንፈታቸው መንስኤ ነው። የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች አንዱ የሚናገረውን ሌላው ማፍረስ (መድረኮችን ያስተውሏል)፣ ተዓማኒነታቸውን አሳጥቶታል።

<u>የኢህአዴግ አሸናፊነት ሚስጥር፡-</u>

ሄኖክ የማነ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ግራውንድ ቴክኒሻን ነው። ሁሌም በምናደርጋቸው የሻይ ቡና ጭውውቶች ገዢው ፓርቲ በተቃዋሚዎች ድክመት ሳቢያ "አይተኬ" የሚሆንበት ደረጃ ላይ ደርሷል ሲል ይሞግተኛል። እንደ ፀሀፊው እምነት በአሁኑ ተጨባጭ ሁኔታ የድርጅቱ "ምትክ አልባነት" ከራሱ ከድርጅቱ የኋላ የታሪክ

የሚመነጭ ነው:: በኢህአዴግ አባል ፓርቲዎች መካከል ያለው የትግል ታሪክና ተሞክሮ የተለያየ ቢሆንም፣ ድርጅቱ ፈተናዎች ባጋጠሙት ወቅቶች ሁሉ እየጠነከረ ሲወጣ የታየ ድርጅት ነው::: እዚህ ላይ የአንድ ፓርቲ ጥንካሬ የሚፈተሸው ሁሉ ነገር በሰመረበት ጊዜ ሳይሆን ፈታኝ ወቅቶች በተጋረጡበት ልክ እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል:: ህወሓት ውስጥ የነበረው ህንፍሽፍሽ፣ ከቀድሞው ኢህዴን እስከ ትላንትናው የድርጅቱ መበስበስና የኢህአዴግ አባል ድርጅት በሆነው ተሃድሶ ድረስ ኢህአዴግ ያጋጠሙት ፈተናዎች የጥንካሬው ምንጮች ናቸው ሆነው አልፈዋል:: ይህ የድርጅቱ ልዩ ባህሪ ነው::

እንደ ሀገርም እንደ ህዝብም የሻዕቢያ ወረራ ሲከሰት ድርጅቱን ያጋጠመው ከላይ የተጠቀሰው አደጋ ድርጅቱን አልገደለውም:: አጋጣሚው ከኤርትራ ጋር የነበረንን ግንኙነት ፈር እንዲይዝም ዕድል ፈጥሯል የሚል ዕምነት አለኝ:: በ1997 ምርጫ ኢህአዴግ የህብረተሰቡን አንዳንድ ክፍሎች ቅሬታ ባለመስማቱና የጀመረው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት የተጠበቀውን ውጤት ባለማስመዝገቡ በመራጩ ካርድ ቢቀጣም አሁን እንደታየው ግን ይህ ሁኔታ ድርጅቱን አጠናከረው እንጂ አላዳከመውም:: ስለሆነም የኢህአዴግ እና አባል ድርጅቶቹ የድሮም ሆነ ዘንድሮ ጥንካሬ ሚስጥር ምንም አይነት አደጋ ቢገጥማቸው ከስህተታቸው መማራቸው እና አለመድገማቸው ነው:: ኢህአፓ ስንቴ ተሳሳተ አሁን የት አለ? መኢሶንስ? ምዕራባዊያን ከቀድሞው ቅንጅት መፍረስ ወዲህ የኢህአዴግ ዋነኛ ተቀናቃኝ ነው በማለት የሚያንቆለጳጵሱት መድረክስ? እነዚህ ወገኖች ከስህተታቸው ተምረው ተጠናክረው ሲወጡ የታዩበት ወቅት ብዙም ትዝ አይለኝም:: ድንጋይ ሁለቴ እንቅፋት ከመታህ ድንጋዩ አንተነህ ያለው ሰው ኢትዮጵያዊ ነው? ማን ነው?

ወደ ዘንድሮው ምርጫ ስኬት ስንመለስ ኢህአዴግ በዝረራ ያሸነፈበት ዋናው ሚስጥር "ሚስጥረ-ምን" አድርጎ መመልከት አይገባም:: የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ምክንያት ለምርጫው በሁሉም ረገድ የተዘረዘረ ፖሊሲና ስትራቴጂ ይዞ መቅረቡ፣ ይህን ተግባራዊ በማድረግ ሀገራችንን ከድህነት ለማውጣት የቆረጠና ከላይ እስከ ታች በዲሲፕሊን የታነፀ አደረጃጀት ስላለው ነው:: የገዢው ፓርቲ ኃላፊነት የመረከብ ብቃት ከዚህ ይመነጫል:: ከዚህም በተጨማሪ ኢህአዴግ የህዝቡን ቅሬታ በመገንዘብ ጉድለቶቹን በማረም ለዘንድሮ ምርጫ መዘጋጀት የጀመረው በ1997 ማግስት መሆኑንም መገንዘብ ይገባል:: ከዚህ ምርጫ በኋላ ፓርቲው በራሱ ውስጥ ያደረገው ግምገማ፣ ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ጨምሮ ከፍተኛ የፓርቲው አመራሮች ከተለያዩ የህብረተሰቡ አካላት ጋር በመገናኘት የህዝቡን ቅሬታ ማዳመጣቸው፣ ፓርቲው በወጣቶችና ሴቶች ዙሪ የሠራው ሰፊ ስራ ለዘንድሮው ስኬት ትልቅ ግብዓቶች ናቸው:: ኢህአዴግ የዘንድሮውን ምርጫ ሠላማዊ፣ ዲሞክራሲያዊና ተዓማኒ ለማድረግ ሲንቀሳቀስ

እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ዝግጁ ነበርና አሸናፊነቱን በተመለከተ ማንኛውም ወገን ምንም ጥርጥር አልነበረውም፡፡

## <u>ይህ ህዝብ ከየት መጣ?</u>

በቅርቡ አውራምባ ጋዜጣን ሳነብ በአንድ ፀሀፊ የቀረበ ጽሁፍ ርዕስ በግርድፉ ህዝቡ የት ሄደ? (ትክክለኛውን ርዕስ ባለማስታወሴ ይቅርታ) በሚል ቅንጅት ለ1997 ምርጫ ሚያዚያ 30 ላይ ያካሄደው ሰልፍ ዘንድሮ ባለመደገሙ በቅሬታ መልኩ ይሁን በመመጻደቅ ላቀረቡት ፅሁፍ የሰጡት ርዕስ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የአዲስ አበባ ነዋሪ ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም በድንገት በአንድ ምሽት በተካሄደለት ጥሪ በመስቀል አደባባይ ጠጠር መወርወሪያ እስኪጠፋ ድረስ ጢም ብሎ በመሰባሰብ በምርጫ ሽፋን እንዳለፈው ህይወቱን ለመገበር ፍላጎት እንደሌለው በመግለፅ ለዲሞክራሲና ለሠላም ያለውን ቁርጠኝነት አሳይቷል፡፡ ህዝቡ ኢህአዴግ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ኢትዮጵያን የሚመራ ፓርቲ እንዲሆን በወል መግባባት እንደመረጠው በይፋ አሳይቷል፡፡

በዚህ ሰልፍ ላይ ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እንዳሉት በ1997 ምርጫ የከተማው ህዝብ ድርጅቱ ከቆመለት ዓላማ ጋር የማይጣጣሙ ተግባሮችን አይቶ በማዘን ድምፁን በመንፈጉ ቢሸነፍም ገዢው ፓርቲ ድክመቱን ለመሸፋፈን ሰበብ ከመፈለግ ይልቅ የህዝብ ቅሬታን ያለአንዳች ማቅማማት በመቀበል ባደረገው መሻሻል አሁን ህዝቡ ዕርካታውን መግለፁን አብስረዋል፡፡ በዚህም ኢህአዴግን ሲመርጥ፤ ተቃዋሚዎችን በምንም ስያሜ ይጠሩ ቀጥቷቸዋል፡፡ ስለሆነም ሚያዚያ 30 ሆነ ግንቦት 17 ህዝቡ ተቃዋሚዎችን ደግፎ ሠልፍ ያልወጣው ስላልጠሩት ሳይሆን የቀጣቸው በመሆኑ ህዝቡ "የት ደረሰ ብለን" ልንጨነቅ አይገባም፡፡ በዚህ ሰልፍ የአዲስ አበባ ነዋሪ በአምስት ዓመት ልዩነት ውስጥ ኢህአዴግን መርጦ ድምጼ ይከበርልኝ ሲል በይፋ ጠይቋል፡፡ ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በሰልፉ ላይ በፍፁም ኢትዮጵያዊ ጨዋነት ባደረጉት ንግግር ህዝቡ በሉዓላዊ የመሾም እና የመሻር ስልጣኑ ለሰጠው ብይን ዝቅ ብለው እና ባርኔጣቸውን አውልቀው በፍፁም ትህትና እጅ ቢነሱ አይበዛበትም፡፡ ጠ/ሚኒስትሩ በዚህ ወቅት ያደረጉት ንግግር አሸናፊው ወገን ሁሉንም ማድረግ በሚችልበት በአፍሪካ ፖለቲካ ሳይቀር ታላቅ የመቻቻል እና በጋራ የመስራት አስፈላጊነትን ይህም እንደሚቻል አስተምረዋል፡፡

## <u>ምርጫ ወዲህ ትዝብት ወዲያ</u>፡-

የተለያዩ ወገኖች ከአገራዊው ምርጫ ጋር ተያይዞ የማጥላላት ዘመቻ ሲያካሂዱ ቆይተዋል፤ ዛሬም አላቆሙም፡፡ የእነዚህ ውግዘቶች ዋናው ምክንያት ገዢው ፓርቲ በምርጫው ቢያሸንፍ እንኳ የምርጫውን ሂደትና ውጤት በማጣጣል ተዓማኒነት

ማሳጣት ነው። ከተቻለም ገዢውን ፓርቲ በማስጨነቅ ከተቃዋሚዎች ጋር እንዲደራደር በማድረግ ስልጣን መጋራት አልያም የእነሱ ደጋፊዎች የሆኑ የውጭ ኃይሎች ሎሌ እንዲሆን ማስቻል ነው። የውጭ ኃይሎች ይህን ስህተት የሚሰሩት አካሄዳቸው ከኢትዮጵያውን አትንኩን ባይነት አስተሳሰብ ጋር የማይሄድ መሆኑን ሊገነዘቡ ባለመቻላቸው ነው። ኢትዮጵያውያን በእንደዚህ አይነት የከፋ ድህነት ውስጥ እንኳ ሆነው ተፅዕኖ እና እጅ መጠምዘዝን ከመቀበል ሞትን የሚመርጡ መሆናቸውን ማወቅ ይገባቸዋል። ኢትዮጵያዊ ስነልቦና ይህን አይፈቅድምና። ስለሆነም ጥምር መንግስት መስርቱ፣ ዕርዳታ እንቀንሳለን ... ወዘተ በማለት ህዝቡን ማስገበር እንችላለን የሚሉት እነዚህ ወገኖች የኢትዮጵያ ፖለቲካ የይግባኝ ፍርድ ቤት እንዳልሆኑ በማያወላዳ መልኩ ሊረዱ ይገባል።

በዚህ ረገድ የምርጫው ሂደት በሠላም ተጠናቆ ጊዜያዊ ምርጫ ውጤት ይፋ ከመሆኑ በፊት "የመንግስት ጭቆና ድምፅ የመስጠት ሂደቱን ዋጋ አሳጥቶታል" ሲል መግለጫ ያወጣው የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል ባዩ ሂዩማን ራይትስ ዎች የተባለ ድርጅት ነው። ድርጅቱ ምርጫው ላይ ላዩን ስርዓት ያለው ቢመስልም መንግስት መራጩን አስገድዷል፤ ተፅዕኖም አሳርፎባቸዋል ሲል ተሸቀዳድሞ መግለጫ ሲሰጥ ዋና ዓላማው በአፍሪካ ህብረት፣ በአውሮፓ ህብረት እና በኢትዮጵያውያን ሲቪክ ማህበራት ታዛቢ ቡድኖች ሪፖርቶች ላይ ተፅዕኖ ማሳደር እና በቀጣይ ለሚካሄድ ዘመቻ ፈር ለመቅደድ ነው። ለእኔ እስከሚገባኝ ድረስ የተፃፈበትን ቀለም ያህል ዋጋ የሌለው ይህ ፅሁፍ "ኢትዮጵያውያን መሪዎቻቸውን መምረጥ አይችሉም" ከሚል ዘረኛና ጊዜ የመሸበት አመለካከት የመነጨ ነው። ከዚህም በመነሳት በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ተፅዕኖ ማሳደር ቢፈልጉ እስካሁን የመጡበት የራሳቸው አላማ አላቸውና አያስደንቅም። ኢትዮጵያውያን ለዲሞክራሲ እንግዳ ይሁኑ እንጂ ባለፉት ጥቂት ዓመታት እያዳበሩት ላለው ዲሞክራሲዊ ባህል ባዕድ አይደሉም። ህዝቡ ዲሞክራሲያዊና ተዓማኒነት ባለው ምርጫ ኢህአዴግን መምረጡ እንዴት ስህተት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል?

ድርጅቱ ኢትዮጵያን በተመለከተ ከወራት በፊት ባወጣው ተመሳሳይ መግለጫ ለጋሾች ለሀገራችን የሚሰጡትን ድጋፍ እንዲያቆሙ ሲጠይቅ የነበረ ከመሆኑ አንፃር ምርጫውን ተከትሎ ያወጣውን ሙሉ በሙሉ አሉታዊ የሆነ መግለጫ የዚህ አካል አድርጌ ነው የማየው። መቀመጫው ዋሽንግተን የሆነው "አፍሪካናይዜሽን ማህበር" መስራችና ሊቀመንበር ሚስተር ኮፊ አክፖንግ የሀገራችንን ምርጫ ሂደት በተመለከተ በሰጡት አስተያየት "ማንም ምንም አለ በምርጫው ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ አፍሪካዊያንም ኮርተዋል"። በኢትዮጵያ መንግስት የተጋበዘው የአፍሪካ ህብረት እና የኢትዮጵያ ሲቪል ተቋማት ምርጫውን ተከትሎ ባወጣቸው መግለጫዎች ከአንዳንድ

ሊታረሙ ከሚገባቸው ጉድለቶች በስተቀር ምርጫው የኢትዮጵያን ህዝብ ፍላጎት ያንፀባረቀ፣ ነፃና ፍትሃዊ ማለታቸው ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ከፍተና ድል ነው።

የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ ምርጫውን አስመልክቶ ላወጣው ሪፖርት የሰጠው ርዕስ «ሰላማዊ እና ሥነ-ሥርዐቱን በጠበቀው የምርጫ ቀን፣ ብዛት ያሳየው የመራጮች ቁጥር በጠባብ ፖለቲካዊ ምህዳርና እኩልነት በጎደለው መድረክ በጥቂቱ ችግሮች አሳይቷል» የሚል ሲሆን የሪፖርቱ ዋና ዋና ይዘቶቹ የሚከተሉት ናቸው:-

- በአጠቃላይ ምርጫው ሠላማዊ በሆነ መልኩ መጠናቀቁን፣
- የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ምርጫውን በበቂ ሁኔታ አደራጅቶታል፣ አስተዳድሮታል፣ መርቶታል ይሁን እንጂ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በምርጫ ቦርድ ገለልተኛነት ላይ የሚያነሱትን ጥያቄ ሊያስወግድ አልቻለም፣
- በተለያዩ አካባቢዎች ውስጣዊ መጨናነቅ የምርጫ ቀን ሲቀርብ እየጨመረ ቢመጣም ምርጫው ሠላማዊ ነበር፣
- ሚዲያው አድሏዊነትን ባላካተተ ሁኔታ የየፓርቲዎቹን እንቅስቃሴ ዘገባ ያካሄደው በማለት መልካም መሻሻሎች ቢተዋወቁም "ምርጫው የተወሰኑ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን" እንዳላሟላ ይገልጻል።
- ከዚህም በተጨማሪ በብዙ አካባቢዎች በገዢው ፓርቲ እና የመንግስት አስተዳደሮች መሀከል ያለው ልዩነት የደበዘዘ እንደነበር፣ ከ1997 በኋላ ዋና ዋናዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መፍረክረካቸው፤ ዋንኞቹ የፖለቲካ ሰዎችም ሀገር መልቀቅ የፖለቲካ ምህዳር ጥበት ሲፈጥር፣ የቪ.ኦ.ኤ ሞገድ መታገድም ህዝቡ ከተለያዩ ምንጮች ሊያገኝ የሚገባውን መረጃ ሊያጣ ችሏል የሚሉ አስተያየቶች የሪፖርቱ አካል ናቸው ናቸው።

ከዚህ ሪፖርት መረዳት እንደሚቻለው ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ለማካሄድ የሚያስችል የህግ፣ የአስተዳደርና ሌሎች መዋቅሮች ያሏት በመሆኑ ሠላማዊ፣ ዲሞክራሲያዊና ተዓማኒ ምርጫ ለማካሄድ በመቻሏም ገዢውም ሆነ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሊኮሩ ይገባል።

እንደዚህ ፀሀፊ ዕይታ ታዛቢ ቡድኑ የጠቀሳቸው ጉድለቶች ተገቢ ናቸው ሊባሉ የሚችሉ ቢሆኑ እንኳ "ምህዳሩ ጠቧል" በሚል የደረሰበት መደምደሚያና አጠቃላይ ሁኔታ ከላይ ከተዘረዘሩት አዎንታዊ አስተያየቶች ጋር የሚጣጣም አይደለም። የቀረበው ድምዳሜ ከአውሮፓውያኑ የፖለቲካ ሂደት፣ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ ባህል እና ወግ እንጂ 20 ዓመት እንኳ ላላስቆጠረው ከኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ሂደት ጋር የሚጣጣም

አይደለም፣ ሊሆንም አይችልም:: አብዛኞቹ ውስን ግድፈቶች ዲሞክራሲያዊ ምርጫን ከማካሄድ ልምድ ማነስ እንጂ ከፖለቲካ ቁርጠኝነት አለመኖር የተፈፀሙ ችግሮች አድርጌ አልወስዳቸውም:: በምርጫ ቦርድ፣ በፖሊስ እንዲሁም በፍትህ አካላት ላይ የተቃዋሚ ፓርቲዎች እምነት ማጣት የግለሰቦች የግል አመለካከቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ እየታወቀ ለፖለቲካው ምህዳር መጥበብ እነዚህ ምክንያት ሆነው ሊቀርቡ አይችሉም:: ከ1997 ምርጫ በኋላ "መንፈስ" ነን ሲሉ ለነበሩ የተቃዋሚ ፓርቲዎች "ነፋስ መግባት እና መፈራረስ" ኢህአዴግ እንዴት ተጠያቂ ተደርጎ ይወሰዳል? አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች የነበሩ ግለሰቦች ከሀገር ከወጡ በኋላ በፍላጎታቸው ባይመለሱ በነዚህ ሰዎች ወደ አገር ውስጥ አለመመለስ ጉዳይ ላይ ምህዳሩ ጠቧል ሲል የአውሮፓ ህብረት ታዛቢ ቡድን ሲገልፅ እነማን መሆናቸውን በግልፅ ቢነግረን በወደድን:: ከእነ ኢንጂነር ኃይሉ፣ አቶ ልደቱ፣ ኢንጂነር ግዛቸው ... ወዘተ ጋር የነበሩትን ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ከሆነ ግንቦት ሰባት ራሱን ከዲሞክራሲያዊና ሰላማዊ ትግል ማግለሉን ታዛቢ ቡድኑ ሊዘነጋ አይገባም:: አለበለዚያ አሁን ያሉ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ዶ/ር ብርሃኑን ሊመጥኑ የሚችሉ አይደሉም ማለት ከሆነ በሀገራችን የፖለቲካ ዓላማዎችና ተሳትፎ ከግለሰቦች ተክለሰውነት ይልቅ በፓርቲዎች ፖሊሲ እና ስትራቴጂ አማራጭ ላይ የተመሠረተ መሆኑን አለመገንዘብ ነው:: የተዛቢው ቡድኑ በቅርቡ ያወጣውን የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት የመጨረሻ አድርጎ እንኳ ቢያወጣ ኢህአዴግ ዋናውን ይሁንታ ከኢትዮጵያውን አግኝቷልና ብዙም ሊያሳስበውና የቃላት እንካ ሰላንታ ውስጥ መግባት አያስፈልገውም:: ስለምን የአምስት ዓመት የብቃት ማረጋገጫ ካርዱን ከ25 በመቶ ተጨማሪ ቦነስ ጋር ከኢትዮጵያ ህዝብ አግኝቷል:: አራት ነጥብ::

<u>ተቃዋሚዎችና ኢህአዴግ የት? ወዴት?</u>

ተቃዋሚ ፓርቲዎች እና ኢህአዴግ መንታ መንገድ ላይ ይገኛሉ:: ለእኛ ተሸናፊም አሸናፊም ፓርቲዎች ሁለቱም ያስፈልጉናል:: በፓርላማው ውስጥ ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ወንበር እንዲኖራቸው ፍላጎት ያላቸው ብዙ ወገኖች ቢኖሩም ምርጫ ማስተዛዘኛ ቁጥር ያለው ሎተሪ ስላልሆነ ሌላ አምስት ዓመት መጠበቅ የግድ ይላቸዋል:: ፓርላማ ውስጥ ቢያንስ አንዳንድ ቅሬታ የሚተነፍስ የተቃዋሚ ፓርቲ አለመኖሩ እነ የተከበሩ አቶ ልደቱ፣ አቶ ቡልቻ፣ ዶ/ር መረራ ... ወዘተ የሚናፍቁን ቀን ይመጣ ይሆን? እዚህ ላይ የተቃዋሚ ፓርቲዎች በፓርላማ ያላቸው ወንበር ቢቀንስም ኖሯቸውም ቢሆን ወንበር ከመያዝ በዘለለ ምን ያህል አገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ሀሳቦች አንስተው ክርክር እንዲካሄድ አስችለዋል፣ አባሌ ታሰረ፣ ተንገላታ፣ ጠ/ሚኒስትሩ መቼ ነው ስልጣን የሚለቁት .... ወዘተ ከሚሉ ጥያቄዎች የዘለለ ሀሳብ ነበራቸው ወይ ብሎ ማንሳት ይኖርብናል:: ስንቶቹ መሪዎችስ ናቸው የፓርላማውን የስብሰባ ጊዜ አክብረው

በስነ ሥርዓት ይሳተፉ የነበሩት? ይህ የአደባባይ ሚስጥር ነው፡፡ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አለመኖር የፓርላማውን ክርክር አያደበዝዘውም በሚለው የጠ/ሚኒስትር መለስ አቋም ላይ ብስማማም በኢህአዴግ የተሞላው ፓርላማ የአስፈፃሚውን አካል የመቆጣጠር ተግባሩን እንዴት እንደሚወጣ ሊታሰብበት የሚገባ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ከልምድ ማየት እንደሚቻለው የገዢው ፓርቲ አባላት ፓርላማ ውስጥ ይህን ሲያደርጉ አላየንም እና፡፡ እንደ እኔ እይታ የተቃዋሚ ፓርቲዎቻችንን በተመለከተ ወደፊት ሁለት የተለያዩ ክስተቶች ይታዩኛል፡፡ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በፓርላማ ወንበር የሌለው ፓርቲ የጎላ እንቅስቃሴ የማድረግ ልምድ የለውም፡፡ አንዳንዶቹ ፓርቲዎችም ከግለሰቦች ሰብዕና ጋር የተያያዙ በመሆናቸው በቀጣዩ ላይዘልቁ በመቻላቸው ሊታሰብ ይገባዋል፡፡ መኢአድ ያለ ኢንጂነር ኃይሉ፣ ኢዴፓ ያለ የተከበሩ አቶ ልደቱ፣ ኦህኮ ያለ ዶ/ር መረራ... ወዘተ የታሰቡ ይሆን? መድረክን ይዞ የቆየው ሰም ጥምረቱን ምን ያህል ቆልፎ ያቆይ ይሆናል? እስካሁን በነበረው ሂደት ሊቀምንብርናውን የተከበሩ ዶ/ር መረራ እና ፕሮፌሰር በየነ እየተፈራረቁ ይያዙ እንጂ ከውስጡ አንዳንድ ፓርቲዎች እየለቀቁ በመሆናቸው ስብስቡ በአንድነት ፓርቲ ይዋጣል አልያም ይፈርሳል ብሎ ማሰብ ይቻላልን፡፡

ሁለተኛ ወደፊት ኢህአዴግን ሊወዳደር የሚችል ስንት ፓርቲ ሀገራችን ያስፈልጋታል? የሚለው ጥያቄ ቢነሳ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ማንም ወገን የመደራጀት መብት ይኑረው እንጂ የፖሊሲ አማራጭ የሌላቸው ስልሳ ምናምን ፓርቲዎች ምንም ትርጉም የላቸውም፡፡ ስለሆነም ተቃዋሚዎች ቆም ብለው እንዲያስቡ ይህ ምርጫ ዕድል ኣፕታቿል፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በምርጫው ውጤት እንደተደናገጡ ሰሞኑን የነበረው ዝምታቸው ብዙ ይናገራል፡፡ ይሁን እንጂ ኢህአዴግ በ1997 እንዳደረገው እነሱም ዘንድሮ ህዝቡ ያልወደደላቸውን ወይም የቀጣቸውን ምክንያት በሰከነ አዕምሮ በመቀበል የህዝቡን ፍትሃዊ ዳኝነት በመቀበል ለ2007 መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ እነሱ ያሸነፉበት ምርጫ ፍትሃዊ፣ የህዝብ ይሁንታ የተገለፀበት ሱናሚ፤ ኢህአዴግ ያሸነፈበትን ደግሞ የተጭበረበረ እንደሆነ በመግለፅ ምርጫውን እንደ ህፃን ጨዋታ በመውሰድ ይደገም ማለት አያዋጣቸውም፡፡ ተቃዋሚዎች ይልቁንም ኢህአዴግንና ለርሱ ድምፁን የሰጠውን ህዝብ እንኳን ደስ አላችሁ እንዲሉ እንጠብቃለን፡፡ ይህ አካሄድ የሰለጠነ በመሆኑ ለዲሞክራሲ ግንባታ አንድ እርምጃ ይሆናል፡፡ የህዝቡን መሪዎችን የመምረጥ ሉዓላዊ ስልጣንም ማክበራቸውን ያሳያል፡፡

ኢህአዴግ አሸናፊ ፓርቲ ነው፡፡ ድርጅቱና አባላቱ በተገኘው ድል ቢደሰቱም ከባድ ፈተና ከፊታቸው ተደቅኗል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በርካታ ጉድለቶች እንዳሉብን እንገነዘባለን ያሉትም ለዚህ ነው፡፡ ኢህአዴግና አባሎቹ የአሁኑ ውጤት ህዝቡ እስካሁን ለተገኙት ድሎች የሰጠው የክንውን ማረጋገጫ ሠርተፊኬት ብቻ መሆኑ ሊዘነጉ

አይገባም፡፡ አሁን የተሰጠው ኃላፊነት ርስት አይደለም፡፡ አነስተኛ ቢሆኑም ተቃዋሚዎችን የመረጠ ህዝብ አለና በተለያዩ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ኢህአዴግ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በማማከር መወሰኑ ብልህነትም አርቆ አስተዋይነትም ነው፡፡

ኢህአዴግ መራሹ መንግስት በቀጣይ በተለያዩ መስኮች ከተገኘ ውጤት በላይ በማስመዝገብ የልማት ጥማቱን ማርካት ብቻ ሳይሆን ድህነትን ትርጉም ባለው መልኩ መቅረፍ ይጠበቅበታል፡፡ ኢህአዴግ እስካሁን የተካሄዱ የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ጥረቶች ስር እንዲሰዱና የጤና፣ የትምህርት፣ የመሠረተ ልማት ግንባታ ጥረቱ የበለጠ እንዲሳኩ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በዲፕሎማሲውም መስክ ያለውን ስኬት ጠብቆ ከመቆየት በዘለለ የሀገራችንን ብሄራዊ ጥቅም ማስጠበቅና በዓለም አቀፍ መድረኮች ተሰሚነታችንን የበለጠ ማጠናከር ይገባዋል፡፡

እንደ ፀሀፊው አመለካከት ኢህአዴግ በቀጣይ ሊጋፈጣቸው ከሚገቡ ችግሮች ውስጥ የመልካም አስተዳደር እና የፍትህ ስርዓት ችግሮች ዋንኞቹ ናቸው፡፡ በሲቪል ሰርቪሱም ውስጥ የህዝብ አገልጋይነትን መንፈስን ማንገስ ይጠበቅበታል፡፡ ሙስናም ከፍተኛው አደጋ ነውና ከራሱ አባል ጀምሮ በጽናት በህጋዊ መንገድ መዋጋት ይኖርበታል፡፡

ድርጅቱ ከመተካካት ተልዕኮው ጋር በተያያዘ የያዘው ዕቅድ ተግባራዊነትና ስኬትን በማረጋገጥ ድርጅቱ "የወደፊቱ ትውልድ ፓርቲ" መሆኑንም ማሳየት አለበት፡፡ እገሌን ማን ይተካል? ከበረሃ ጀምሮ የመጣውን ነባር አመራር የሚተካው ትውልድ አካል እነማን ይሆኑ? ድርጅቱን በቀጣይ ማን ይመራ ይሆን? እነዚህ መሪዎች ለ2007 ምርጫ አሁን በሃላፊነት ያሉትን ያህል ይመጥኑ ይሆኑ? ወደፊት የሚታይ ጉዳይ ይሆናል? ሠላም፡፡